# የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ቤተሰቦች የ2025-26 የይግባኝ መመሪያ

የከፍተኛ ችሎታ ያላቸው አገልግሎቶች(HC) ዲፓርትመንት(Highly Capable Services (HC)department)ከየይግባኝ ሂደት በፊት፣ወቅት እና በኋላ መመሪያ ለመስጠት ይጥራል (WAC 392-170-076)።ቤተሰቦች ተማሪያቸውን ለአገልግሎቶቹ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ይግባኝ ማለት ይችላሉ።ቤተሰቦች ልዩ ሁኔታዎችን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ማቅረብ አለባቸው።

ይግባኙ ከሰነዶች/ማስረጃዎች ጋር (ለይግባኝዎ አስፈላጊ ከሆነ) አንዴ ከገበ በኃላ፣HC ዲፓርትመንት በየይግባኙ የግምገማ ወቅት ከግምት ውስጥ የሚገቡ ተጨማሪ መረጃዎችን ወይም ሰነዶችን አይቀበልም።

**የይግባኙ ቅፆች እስከ አርብ፣የካቲት 20፣2026 መግባት አለባቸው።**

## ለመጀመር

ይግባኝዎን ከማቅረብዎ በፊት፣እባክዎ የሚከተሉትን ሰነዶች ለማግኘት ትንሽ ጊዜ ይውሰዱ:

☐የተማሪ የብቁነት ደብዳቤ።ይህ ደብዳቤ/ውጤት በየSource account መለያዎ ይገኛል።

☐ስለ የይግባኝ ዓይነቶች እና የጊዜ ገደብ መረጃ።
- በየከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ድር ገጽ(Highly Capable web page) ላይ ይገኛል።

☐ የይግባኝ ቅጹን (Appeal form) ይሙሉ።በተማሪዎ የብቁነት ደብዳቤ ላይም ይገኛል።

☐የይግባኝ ቅጹን ካቀረቡ በኋላ **በ24 ሰአታት** ውስጥ ልዩ ሁኔታውን የሚያብራሩትን መግለጫ እና ከአስተማሪዎች የሚመጡ የድጋፍ ሰነዶችን ማቅረብ።
- ይህን መረጃ ወደ hicap2@seattleschools.org መላክ አለብዎት።ሂደቱ ቀላል እንዲሆን በርእስ መስመሩ **"Appeal"** ብለው ይፃፉ።

የይግባኝ ቅጹን ለመሙላት የትርጉም አገልግሎቶች የሚፈልጉ ከሆነ፣እባክዎን የከፍተኛ ችሎታ ያላቸው አገልግለቶች ዲፓርትመንት የደንበኞች እንክብካቤ ቡድንን በ hicap2@seattleschools.org ያነጋግሩ።

## ይግባኙን ማጠናቀቅ

ቤተሰቦች ይግባኝ ለማለት ከሁለቱ አማራጮች አንዱን መምረጥ አለባቸው:**ሁኔታዊ (Conditional)** ወይም **መለየት(Identification)**።

ይግባኝዎ በእነዚህ ሁለት ምድቦች ውስጥ የማይካተት ከሆነ፣ይግባኝዎ አይገመገምም፣እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለዚህ መረጃ የማሳወቂያ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል።

**ሁኔታዊ ይግባኝ(Conditional Appeals)**
ሁኔታዊ (A condition ወይ circumstance) መረጃውን ትክክለኛ እንዳይሆን ወይም እንዳይገኝ አድርጎታል ተብሎ ከታመነ።

- ምሳሌ1: ተማሪዬ በ የMeasure of Academic Progress (MAP) assessment የፈተና ጊዜ በሙሉ ከታመመ፣እና ይህም በየዶክተር ማስረጃ እና በየርእሰ መምህር ደብዳቤ ከተረጋገጠ።
- ለምሳሌ 2: የተማሪዬ አይፓድ በፈተናው ወቅት በሌላ ተማሪ ተወሰዶ ነበር።ይህ ወዲያውኑ ለአስተማሪው ሪፖርት ተደርገዋል፣ እሱም በርዕሰ መምህሩ ሁኔታውን ተረጋግጧል።

**ይግባኝ አቅራቢው አካል የሚከተሉትን መሰብሰብ እና በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡**
በሁኔታው ምክንያት የተማሪያቸውን የመለያ ውጤት ትክክል እንዳይሆን አድርጎታል ብለው የሚያምኑበትን ምክንያት የሚገልጽ ማብራሪያ እና ማስረጃ እንዲሁም ለተማሪያቸው ለምን የተለየ ነገር መደረግ እንዳለበት አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ።

**የመለየት ይግባኝ(Identification Appeals)**
ለመለየት ጥቅም ላይ በዋለው መረጃ ውስጥ ስህተት ነበረው።ይህም ተማሪው ለአገልግሎቱ ብቁ ሆኖ እንዳይገኝ አድርጓል።

- ለምሳሌ: መምህሩ እና ርእሰ መምህሩ የግምገማው መረጃ በስርአቱ ውስጥ በትክክል አለመጫኑን ካረጋገጡ።

**ይግባኝ አቅራቢው አካል የሚከተሉትን መሰብሰብ እና በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡**
ለመለየት ጥቅም ላይ በዋለው መረጃ ላይ ስህተት መኖሩን የሚያረጋግጥ በማስረጃ የታጀበ ማብራሪያ።.

**ቀጥሎ ምን ይሆናል?**

ይግባኙ  አንድ ጊዜ ከቀረበ በኃላ፣የብዙ ዲሲፕሊን ምደባ (MPC) የይግባኝ ኮሚቴ ይገናኛል፣እያንዳንዱን የይግባኝ ቅጽ እና የመጀመሪያውን የብቁነት ውሳኔ ለማድረግ ጥቅም ላይ የዋለውን መረጃ ይገመግማል፣ከዚያም የይግባኙ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

የMPC ይግባኝ ኮሚቴ የሰለጠኑ አስተማሪዎች እና ሌሎች እንደ አማካሪዎች፣አስተማሪዎች እና የዲስትሪክት መሪዎች ያሉ ሙያዊ ሰራተኞችን ያቀፈ ነው።ኮሚቴው በይግባኙ የገባውን የተማሪ መረጃ/ማስረጃ ይገመግማል እና ይግባኙን ትክክል መሆኑን ካመነ በየብቁነት ውሳኔ ላይ ለውጥ እንዲደረግ ይወስናል።

ኮሚቴው የይግባኝ ማመልከቻውን ገምግሞ እንደጨረሰ፣የይግባኝ ቅጹን በደረሳቸው በ25 የትምህርት ቀናት ውስጥ ለቤተሰቦች የጽሁፍ ውሳኔ ይሰጣል።

የMPC ይግባኝ ኮሚቴ በዓመት ለአንድ ተማሪ **አንድ** ይግባኝ ይገመግማል።የኮሚቴው ውሳኔ የመጨረሻ ነው።

በክልሉ ህግ መሰረት፣በዲስትሪክቱ ባለስልጣን የመጨረሻውን ውሳኔ ያልተደሰተ ሰው ውሳኔው ከተላለፈ በ30 ቀናት ውስጥ ወደ ኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል።

ተጨማሪ ጥያቄዎች? በhicap2@seattleschools.org ያግኙን።